# በደርግ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተስፋዬ ዲንቃ አረፉ

አባይ ሚዲያ ዜና
ግርማ አለሙ

የኢትዮጲያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢህዲሪ) የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርና ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተስፋዬ ዲንቃ ህዳር 29፣ 2009 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። አቶ ተስፋዬ ዲንቃ ያዴሳ ከ1981 እስከ 1983 በውጪ ጉዳይ ሚኒስትርነት እንዲሁም በደርግ ወታደራዊ መንግስት የመጨረሻዎቹ 3 ወራት በጠቅላይ ሚኒስትርነት አገልግለዋል።

አቶ ተስፋዬ ዲናቃ የተወለዱት አምቦ ከተማ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አምቦ ጨርሰው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት አዲስ አበባ በሚገኘው የውንጌት ት/ቤት ነበር። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ቤሩት በሚገኘው የአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ ሲቀዳጁ፣ በአሜሪካ፣ ሲራኪውስ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ፣ በኢንደስትሪያል ኢንጂነሪንግ፣ የማስትሬት ዲግሪ አግኝተዋል።

በዲሴምበር 7፣ 2016 በ 77 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት፣ በፌርፋክስ፣ ቨርጂኒያ፣ ይኖሩ እንደነበረም ተዘግቧል። አቶ ተስፋዬ፣ ባለትዳር፣ የአራት ልጆች አባትና ለአራት የልጅ ልጆች የታደሉ አዛውንት ነበሩ፡፡